# ምዕራፍ ስምንት

# ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው።

ከሰማያት የወረደው ከድንግል የተወለደው ወልደአብ ወልደማርያም "አምላክ ወሰብእ" ነው። በመሆኑም ራሱን የሰው ልጅ በማለት ጠርቷል የሰው ልጅም ተብሏል፤ የሰው ልጅ (ፍጹም ሰው) መሆኑን የሚያገናዝቡ ጥቅሶች ማቴ 8፥20, ማቴ 9፥6, ማቴ 16፥13, ማር 8፥31, ማር 14፥62, ሉቃ 19፥10, ሉቃ 21፥36, ዮሐ 1፥14, ዮሐ 3፥13, ዮሐ 8፥40, 1ጢሞ 2፥5, 1ጢሞ 3፥16, 1ዮሐ 4፥2-3

## 1. ስለኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውነት መጽሐፍ ቅዱሳውያን ማረጋገጫዎች፤

1.1 በሥጋ የወለደችው እናት እንዳለችው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል (ሉቃ 1፥43, ገላ 4፥4)

1.2 እንደሰው ውኃ ይጠማዋል ልክ እንደ አንድ አይሁዳዊ ፍጹም ሰውነቱ ተገልጿል (ዮሐ 4፥9)

1.3 የሰውን ሥጋና ደም ነፍስንም ስለነሣ በሥጋና በደም እኛን መስሏል(ሆኖአል) (ዕብ 2፥14-16)

1.4 ፍጹም እንደእኛ ያለ ሰውነት (ሰብአዊ አካል) አለው (ማቴ 26፥12)

1.5 እንደማንኛውም ሰው ቀስ በቀስ አድጓል (ሉቃ 2፥40)

1.6 እድሜ ተቆጥሮለታል (ሉቃ 3፥23)

1.7 አላዋቂ ሥጋን በመልበሱ ጥያቄ ጠይቋል (ሉቃ 2፥46)

1.8 በጥበብ አድጓል (ሉቃ 2፥52)

1.9 ጸልዮአል (ማር 1፥35, ሉቃ 11፥1)



1.10 ተፈትኖአል (ማቴ 4፥1-11, ዕብ 2፥18, ዕብ 4፥15)

1.11 መታዘዝን ተምሮአል (ዕብ 5፥8)

1.12 ረኃብተኛውን የሰውነት ባሕርይ እንደነሣ ለማጠየቅ ተርቧል (ማቴ 4፥2, ማቴ 21፥18)

1.13 የሚጠማ ባሕርየ ሰብእን እንደነሣ ለማጠየቅ ተጠምቷል (ዮሐ4፥7, ዮሐ19፥28)

1.14 የሚጨነቀውን የሰዎችን ባሕርይ እንደነሣ ለማጠየቅ ደክሟል (ዮሐ 4፥6)

1.15 ደካማውን ዕረፍት የሚያሻውን ሰብአዊ ባሕርይ እንደነሣ ለማጠየቅ ተኝቷል (ማቴ 8፥24)

1.16 አዝኗል አልቅሷል (ማቴ 9፥36, ማር 3፥5, ዮሐ 11፥35, ሉቃ 19፥4)

1.17 ደስ ብሎታል ሐሴትም አድርጓል (ሉቃ 10፥21, ዕብ 12፥2)

1.18 ተጨንቋል (ማር 14፥33-34, ዮሐ 11፥33, ዮሐ 12፥7, ዮሐ 13፥21)

1.19 የደም ላብ አልቦታል (ሉቃ 22፥44)

1.20 ፍጹም ሰው ነውና ተሰቃይቷል (ስለበደላችን) (1ጴጥ 4፥1)

1.21 ደምቷል (ዮሐ 19፥34)

1.22 ሟች ሥጋን ስለነሣ ሞቶአል (ማቴ 27፥50, 1ቆሮ 15፥3)

1.23 ተቀብሯል (ማቴ 27፥59-60)

ይህ ሁሉ በለበሰው ሥጋ ይፈጸም እንጂ ባሕርየ መለኮቱ ግን ሕያው ስለመሆኑ "ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ፣ በሥጋ ሞተ በመለኮት ግን ሕያው ነው" ተብሎ እንደተጻፈ በመለኮት ሥጋ ሕያው ቢሆንም መለኮት በሥጋ እንደሞተ ነገር ግን ባሕርየ መለኮቱ እንዳልሞተ ልብ ልንል ያስፈልጋል። (1ጴጥ 3፥18)

## 2. የመለኮታዊነቱ መጽሐፍ ቅዱሳውያን ማረጋገጫዎች፤

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እንደመሰከረ የባሕርይ አምላክ (መለኮታዊ) መሆኑንም ያረጋግጣልና የሚከተሉትን ነጥቦች እንመልከት፤

2.1 በሽታ ሁሉ በእርሱ ተሸንፎአል (ማቴ 8፥1, ሉቃ 4፥39)

2.2 አጋንንት ሁሉ ተገዝተውለታል (ማቴ 8፥16, 17፥28-32, ሉቃ 4፥35)

2.3 የሰዎች ልብ ሁሉ ለእርሱ ተሸንፎአል ተከተሉኝ ሲላቸው ያለምንም ጥያቄ ይከተሉት ነበርና (ማቴ 9፥9, ዮሐ 17፥2)

2.4 ፍጥረት ሁሉ ተገዝቶለታል (ማቴ 8፥26)

2.5 ኃጢአትን ሁሉ በሥልጣኑ ይደመስሳል (ማቴ 9፥1-8)

2.6 ኃጢአተኞችንና ቀራጮችን በመቅረብ ከሽማግሌዎች ወግ በላይ መሆኑን ገልጿል (ማቴ 9፥10-17)

2.7 ሞትን ድል ነሥቷል (ሉቃ 7፥14-15, 8፥54-56, ዮሐ 11፥4)

2.8 ሁሉን አዋቂ ነው። ሁሉን አዋቂነቱም

- 2.8.1 በናትናኤል ታውቋል (ዮሐ 1፥48)
- 2.8.2 የይሁዳን ተንኮል በማወቁ ታውቋል (ዮሐ 6፥70)
- 2.8.3 የፈሪሳውያንን ልብ አውቋል (ማቴ 12፥25, ሉቃ 5፥22, ሉቃ 6፥8, ሉቃ 7፥39-40)
- 2.8.4 የጸሐፍትን ሐሣብ አውቋል (ማቴ 9፥3-4)
- 2.8.5 የአንድን ጸሐፊ በጎነት አውቋል (ማር 12፥34)
- 2.8.6 የሳምራዊቷን ሴት ቀዳማዊ ታሪክ አውቋል (ዮሐ 4፥24)
- 2.8.7 የደቀመዛሙርቱን ችግር ያውቅ ነበር (ሉቃ 9፥46-47)

2.9 በሁሉም ሥፍራ ምልዓት መለኮቱ ይገኛል ለምልዓተ መለኮቱ ወሰን የለውም። (ማቴ18፥20, ማቴ 28፥20, ዮሐ 3፥13, ዮሐ 14፥20)

2.10 መላእክት ያመልኩታል (ዕብ 1፥6)

2.11 የሚሰገድለት አምላክ ነው። (ሉቃ 2፥15, ማቴ 2፥2, ማቴ 8፥2, ማቴ 15፥25, ማቴ 9፥18, ማቴ 20፥20, ማር 5፥6, ዮሐ 9፥38)



2.12 ሐዋርያው ቶማስ አምልኮታል (ዮሐ 20፥28)

2.13 በሐዋርያት ተመልኳል (ማቴ 14፥33, ማቴ 28፥9)

2.14 የለበሰው የሰው ልጆች ባሕርይ ከፈታሒነት በአፍአ ሲኖር ሳለ ከወልደ እግዚአብሔር ጋር በመዋሐዱ ፈራጅ አምላክ ሆኖአል። (ዮሐ 5፥2)

2.15 በሥልጣኑ ኃጢአትን አስተስርዮአል (ማር 2፥5, ማር 19፥11)

2.16 በሥልጣኑ ሁሉን ያድናል (ማቴ 18፥11) እንዲያውም ከሰማይ በታች ከእርሱ ሌላ መድኃኒት የለም (ሐዋ 4፥2)

2.17 ቅዱስ እስጢፋኖስም ነፍስ የሚቀበል ጌታ ብሎ ጠርቶታል (የሐዋ 7፥59)

2.18 ጃንደረባው ወልደአምላክ መሆኑን መስክሯል (የሐዋ 8፥37)

2.19 ቅ/ጳውሎስ አምላክ ብሎታል (ሮሜ 9፥5, ቆላ 1፥15-17, ቆላ 2፥9)

2.20 ቅ/ዮሐንስ እውነተኛ አምላክ ብሎታል (1ዮሐ 5፥21-22)

2.21 ቅ/ዮሐንስ መጀመሪያ መጨረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ አምላክ ብሎታል (ራዕይ 1፥8, ራዕይ 1፥17-18, ራዕይ 22፥13)

2.22 ቅ/ጳውሎስ እግዚአብሔር ብሎታል (የሐዋ 20፥28)

ከዚህ በላይ በከፊል የተመለከትናቸው መጽሐፍ ቅዱሳውያን መረጃዎች የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊነት (የባሕርይ አምላክነት) የሚጠቁሙ ናቸው። በመሆኑም ወልደአብ ወልደማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው ያውም ግን በተዋሕዶ።

## 3. ልዩ ስም፤

ከስሞች ሁሉ የላቀ ከስሞች ሁሉ የከበረ ልዩ ቅዱስ ድል አድራጊ ስም፣ ስም አንድን ነገር ከሌላው መለያና እንዲሁም አለ ለተባለ ህልውናው ለታወቀ የሚወጣ፣ የአንድ ሰው መታወቂያና መጠሪያ ነው። ስም የሚወጣው ለሰው ብቻ አይደለም። ለማንኛውም ሕልው ለሆነ ነገር

ሁሉ ለሚታየውም፣ ለማይታየውም፣ ለረቂቁም፣ ለግዙፉም፣ ለውሱኑም፣ ለምሉኡም ይሰጣል። እነዚህ ለልዩ ልዩ ነገሮች የወጡት ወይም ልዩ ልዩ ነገሮች የሚጠሩባቸው ስሞች ግን ልዩ ስም ብለን እንደጠራነው ኃይልን የተቀዳጁ አይደሉም። "ስም አይቀበርም" ቢባልም ጊዜ ሲያስረሳቸው ይዘነጋሉ አሁን ግን ከስሞች ሁሉ የተለየ ስም ስለሆነ ሕይወት መድኃኒት ስለሆነ ስም ነው የምናጠናው። የስሙን ታላቅነት ለመገንዘብ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ይበሉና ያገናዝቡ።

## 3.1 ሁሉን የምናደርግበት ልዩ ስም፤

"እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት" (ቈላ 3፥17) ክርስቲያን ሆይ አንተስ የምታደርገውን ሁሉ በዚህ ልዩ ስም ታደርገዋለህን?

## 3.2 የምናምንበት ልዩ ስም፤

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" (ዮሐ 1፥12)

"የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" (1ዮሐ 5፥13)

"ትእዛዙም ይህች ናት በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ ትእዛዝንም እንደሰጠን እርስ በእርሳችን እንዋደድ ዘንድ።" (1ዮሐ 3፥23) ተብሎ እንደተጻፈ ፍጥረት ሁሉ የሚያምንበት ለሚያምንበትም የልጅነት ሥልጣንን የዘለዓለም ሕይወትን የሚያሰጥ ልዩ ስም ነው።



## 3.3 የምንድንበት ልዩ ስም ነው፤

"መዳንም በሌላ ማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።" (ሐዋ 4፥12) እንደተባለ ከሰማይ በታች ምንም መተኪያ የሌለው መድኃኒት የሆነ ልዩ ስም ነው።

### 3.3.1 ከኃጢአት የዳንበት ልዩ ስም ነው፤

"ልጅም ትወልዳለች እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ" (ማቴ 1፥21) እንዳለ ቅ/ገብርኤል ሉቃ.1፥31 "ወትሰምይዮ ስሞ ኢየሱስ" ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ ተባለ። እንዲሁም በሉቃ. 2፥21 በቤተግዝረት ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ታወጀ። የስሙም ትርጉም መድኃኒት ማለት ነው።

### 3.3.2 ሽባን የሚያድንና የሚያቆም ልዩ ስም ነው፤

"በስሙም በማመን ይህን የምታዩትንና የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው በእርሱም በኩል የሆነው እምነት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና ሰጠው።" (የሐዋ 3፥16) እንዳለ ቅ/ጴጥሮስ

### 3.3.3 አጋንንትን የምናዝዝበት ልዩ ስም ነው፤

"ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው፦ ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል።" (ሉቃ 10፥17, ማር 16፥17) በማለት ሰብዓው አርድዕት እንደመሠከሩ ሉቃስ ጽፎልናል።

## 3.4 ንስሐ የሚሰበክበት ስም፤

"በስሙም ንስሐና የኃጢአት ሥርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል" (ሉቃ 24፥47) እንደተባለ የኃጢአት ሥርየትን የሚሰጥ ልዩ ስም ነው። አንድ ሰው ከሰማይ እሳት ወርዶ ሊበላህ ነው

ዘንዶ ሊውጥህ ነው ምድር ልታሰጥምህ ነው ቢባልና ቢያለቅስ ቢጸጸትም ለሕይወት አይሆነውም ፈርቶ ነው እንጂ የመስቀሉ ፍቅር ገብቶት ለምን ኃጢአት ሠራሁ ብሎ አይደለምና። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ግን አምኖ ንስሐ ቢገባ ይጸድቃል።

## 3.5 <u>ኃጢአታችን የሚሰረይበት ልዩ ስመ ሥርየት ነው፤</u>

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ሥርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።" (ዮሐ <u>10፥43</u>) "ልጆች ሆይ ኃጢአታችሁ ስለስሙ ተሰርዮላችኋልና እጽፍላችኋለሁ" (1ዮሐ<u>2፥12</u>) ተብሎ የተጻፈውም ቃለ እግዚአብሔር ይህንኑ ነው የሚገልጸው።

## 3.6 <u>የምንጸልይበት ልዩ ስመ ጸሎት ነው፤</u>

"አብም ስለወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።" (ዮሐ <u>14፥13-14</u>)

"በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ።" (ዮሐ <u>16፥26</u>) "በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።" ተብሎ ተጽፎአል። (ዮሐ <u>16፥23-24</u>)

ክርስቲያን ወንድሜ ሆይ አንተስ በዚህ ልዩ ስም ትጸልይበታለህን? ጥቅሙንስ አውቀኸዋልን? ኸረ ጸልይበት ይህ ልዩ ስም ያልተጨመረበት ጸሎት በአንተ ስም የምትልከው ጸሎት ወደአርያም አይወጣም ግዳጅም አይፈጽምም። ይህ ስም ያለበት በዚህ ስም ላይ የተመሠረተ ጸሎት ምላሹ ይፈጥናል ግዳጁ ይፈጸማል። የልብን ያደርሳል የሰማይ ደጆች ይከፈቱለታል። አንባቢ ሆይ በአንተ ስም ብዙ የጸሎት ደብዳቤ ወደ አርያም ከምትልክ በዚህ ልዩ ስም ትንሽ ደብዳቤ ብትልክ ይደርስልሃል።



## 3.7 <u>የምናመሰግንበት ልዩ ስም፤</u>

"ሁል ጊዜ ስለሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንና አባታችንን ስለሁሉ አመስግኑ።" (ኤፌ <u>5፥20</u>)

"እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለተሰማች አስቀድሜ ስለሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ።" (ሮሜ <u>1፥8</u>) ብሎ እንደተናገረ ስለሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባል።

ይህ ትምህርት በእናት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተቀባይነት ያለው ቋሚ ትምህርት ነው። ይህን ስም ለጸሎትም ሆነ ለምስጋና በሚጠቀሙ ላይ ዛሬ ዛሬ አንዳንዶች ልዩ ስም እየሰጡ ነው።

ቤተ ክርስቲያን እስከዛሬ የምትገለገልበት የቅዳሴ መጽሐፍ ስንመለከት በዚህ ሕይወት መድኃኒት በሆነ ስም የጸሎቱም ክፍል ሆነ የምሥጋናው ክፍል ያጌጠ ነው። በ14ቱ ቅዳሴያት የመጀመሪያውን ጥራዝ የያዘው የሐዋርያት ቅዳሴ ተብሎ የሚጠራው ቅዳሴ "ነአኩተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ" በአማርኛ "አቤቱ በተወደደ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናመሰግንሃለን" ይላል ሌላም በአመክንዮም በቅዳሴው ሞልቷል።

ነገር ግን አንዳንዶች ቋንቋቸውን ያላወቁ (ግዕዝን) የቤተክርስቲያ ናቸውን መጻሕፍት ያልመረመሩ በቤተክርስቲያን ስም ግን የሚያታልሉ ጥቅም ሐዋርያ ያደረጋቸው ውዳሴ ከንቱ ጻድቅ ቅዱስ ያሰኛቸው የምሥጢር ሳይሆን የነገር ቁርሎሶች የሃይማኖት አትናቴዎሶች ሳይሆኑ የርግማንና የስድብ አትናቴዎሶች በዚህ ስም ለሚጸልዩም ሆነ ለሚያመሰግኑ ምዕመናን መሰናክሎች ብቻ ሳይሆኑ አሳቾችም ሆነዋል ዛሬ ቤተክርስቲያንን እየከፋፈሉ ያልመሰላቸውን ስም እየቀቡ ወጣቱን የሚያባሉት የቤተክርስቲያን ምሁራን ንጹሐን አበው ሣይሆኑ ሌሎች ሐሣውያን ናቸውና በእነርሱ አንረበሽ ከእውነትም አንሸሽ።

## 3.8 ከስሞች ሁሉ የሚበልጥ ስም፣ የምንበረከክለት ስም፣ ምላስ ሁሉ የሚመሰክርለት ስም፤

"በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለልክ ከፍ ከፍ አደረገው ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው። ይህን በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።" ተብሎ እንደተጻፈ (ፊልጵ 2፥9-11)

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ልዩ ነው። በአንተ ዘንድሳ ትልቅነት ያለው ሞገስ ያለው የምታከብረው ሲጠራ እንኳ ለስም አጠራሩ ክብር ያለው የማን ስም ነው? ጉልበትህስ ኢየሱስ ተብሎ ሲጠራ ሞገስ ላለው ስም ይንበረከካልን? ዕለት ዕለትስ ምላስህ ስለምን ያወራል? ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ፣ መድኃኒት ጌታ እንደሆነ ነውን? ወይስ ስለሌላ ታወራለህ?

አንባቢ ሆይ በል ከስሞች ሁሉ የሚበልጠውን ጉልበት ሊንበረከክለት ምላስ ሁሉ ሊመሰክርለት የሚገባውን ለስም አጠራሩ ምስጋና የሚገባውን ጣዕም ያለውን ስም ሁል ጊዜ በጸሎት በምስጋና በማስተማር ጊዜህ ኢየሱስ ክርስቶስ ብለህ አንሣው፣ ሞገስህ ነውና። ነገር ግን በሆነ ባልሆነው ኢየሱስን በማለት የአምላክህን ስም በከንቱ እንዳታነሣ ልብ በል (ዘጸ 20፥7)

## 3.9 የምንነቀፍበት ስም፤

"ስለክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ።" (1ጴጥ 4፥14) ተብሎ እንደተጻፈው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚገባ የሚወዱ ሰዎች ባልተማሩ፣ ባላወቁ የክርስትና ስሙን እንጂ ሕይወቱን ባልተለማመዱት ይልቁንም



አረማውያን በሆኑ ሰዎች ዘንድ ይነቀፉበታል። ስለዚህ ስምም የሚነቀፉ ሰዎችን ከላይ የተመለከትነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍለ ቃል እንደገለጸልን የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያድርባቸዋል ብፁዓንም ይሰኛሉ።

አንባቢ ሆይ አንተስ ስለዚህ ስም ተነቅፈህ ታውቃለህን? ከተነቀፍክስ ምን ተሰማህ አይዞህ ደስም ይበልህ የክብር መንፈስ የእግዚአ ብሔር መንፈስ በአንተ ይኖራልና መጽሐፍም ብፁዕ ነህ ይልሃልና።

## 3.10 የምንጠላበት ስም፤

"በሁሉ ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ እስከመጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል" (ማቴ 10፥22) እንዲሁም "በሁሉም ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ" (ሉቃ 21፥17) ይላል።

ከመጀመሪያው ምዕት ዓመት እስከ ሦስተኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ቤተክርስቲያንን በሮማ ቄሣሮችና መምለክያነ ጣዖት ዘንድ ያስጠላት ይህ ስም ነበር። መጠላት ብቻ ሳይሆን ሰይፍ አስመዝዞባታል ከአንበሣ ጋር አታግሎአታል፣ ለሰይፍ አፎት ለአንበሣ አንደበት ለሚፈጅ እሳት ዳርጓታል፣ ሆኖም ሌሎችን ለወጠችበት እንጂ አልተለወጠችበትም።

አንባቢ ሆይ አንተስ በዚህ ስም ተጠልተህበታልን? አዎን ካልከኝ ሌላ ጥያቄ ልጨምር ፍቀድልኝ ምናልባት በግል ስሕተትህ ተነቅፈህ ከሆነ የተነቀፍክ በስሕተትህ እንጂ በስሙ አይደለምና የምትነቀፍበትን ነገር ልብ በለው ስለስሙ ከሆነ ግን የምትነቀፈው አይዞህ ታሸንፋለህ እንጂ አትሸነፍበትም።

## 3.11 የተገባቸው የሚናቁበት ስም፤

"ሐዋርያትንም ወደእነርሱ ጠርተው ገረፉአቸው፤ በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው እነርሱም ስለስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ።" (ሐዋ

5፥40-41) ተብሎ እንደተጻፈ ሐዋርያት ስለስሙ ሲነቀፉ ለዚህ የበቁና የተገባቸው ስለሆኑ ደስ አላቸው ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስም መናቅና መነቀፍ የክርስትና ታላቁ ደረጃ መሆኑን ልብ እንበል፣ ያልተገባቸውና ያልታደሉ ክርስቶስ ኢየሱስን በትዕይርተ መስቀሉ አይመስሉትም።

አንባቢ ሆይ አንተስ ለዚህ ማዕርግ ለሐዋርያነት ማዕርግ ደርሰሃልን? ወይስ እንደ አስመሳይ ክርስቲያኖች ወደጠንቋይ በመሄድ፣ በስካር፣ በዝሙት፣ በሐኬት ነው የምትነቀፈው፣ የምትናቀው። ስለኢየሱስ ስም የምትናቅ ከሆንክ ግን በርታ አይዞህ እንደሌቦች በስርቆት፣ እንደጉቦኞች በጉቦ፣ እንደሰካራሞች በስካር . . . ሣይሆን ስለስሙ ስለተነቀፍክ ደስ ይበልህ በሁለተኛው መምጣቱ ጊዜ ስለተነቀፍክበት ስሙ ሲል ከነቀፉ ያድንሃልና።

## 3.12 ከእሥራትም አልፎ ለሞት እንኳ የምንሰጥለት ስም፤

"እያለቀሳችሁ ልቤንም እየሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳ ተሰናድቼአለሁ እንጂ ለእሥራት ብቻ አይደለም።" እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ (ሐዋ 21፥13)

## 3.13 የምንሰበሰብበት ስብሰባችን የሚባረክበት ስም፤

"ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" ብሎ ጌታ በወንጌል እንደተናገረ (ማቴ 18፥20)

## 3.14 ከኃጢአት የታጠብንበት ስም፣ የጸደቅንበት ስም፤ የተቀደስንበት ስም

"ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል ተቀድሳችኋል ጸድቃችኋል።" (1ቆሮ 6፥11) ብሎ ቅ/ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ያበሠረው ይህንኑ ነበር።



## ግብረ ሕማማት (ጥቅስ በግዕዝ)

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ዘበአማን ዘእግዚአብሔር አብ ግበር ምስሌነ ምሕረተ በመንግሥትከ እስመአፈ አቡከ ይከውን ስምዐ ለከ እንዘ ይብል አንተ ወልድየ ወአነዮም ወለድኩከ ኪሩቤልኒ ይቀውሙ ታሕቴከ ወሱራፌልኒ ኢይኔጽሩከ ወንሕነሰ ንሬእየከ ኵሎ ዕለተ በውስተ ምሥዋዕ ቅዱስ ወንነሥእ ሥጋከ ወደመከ ክቡረ፣ ወኵሉ ስባሔ መንፈሳዊ ይደሉ ለከ ኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ዝንቱ ውእቱ ዕብን ዘበአማን ዘኢይትዐወቅ ሤጡ ዘወሀበ ነጋዲ ኵሎ ንዋዮ ወተሣየጦ ግበር ለነሂ ዓዲ ይእዜ ዘንተ ዕብነ ያብርህ ላዕሌነ በብእሲነ ዘውስጥ ሥርጋዌ ነፍስነ ወትፍሥሕተ ልብነ ውእቱ ስምከ ቅዱስ ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኪሩቤል ይጠፍሖ በክነፊሆሙ ይሴብሕዎ ወይዌድስዎ ለእግዚእየ ኢየሱስ ኦ ርኍሩኅ መሐሪ ወመስተሣህል አበ ኵሉ ምሕረት የዐርብ ፀሐይ በጊዜሁ ወአንተሰ አንተ ከመ ወዓመቲከኒ ዘኢየሀልቅ እስመ በአስተሐምሞ ኂሩትከ አፅነንከ ሰማያተ ወወረድከ ኀቤነ ከመ ፀቃቤ ሥራይ ጠቢብ ዘበአማን መፈውስ ፈወስከ ኵሎ ደዌነ ነዕር ኀቤየ ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ በዐይነ ሣህልከ እንተ ዘኂሩትከ ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ስድድ እምኔየ ኵሎ መንፈሰ እከይ እንተ ዘፀላዒ ወረሲ ውስቴትነ ኀሊና ንጹሐ ከመንዘከርከ። ኦድኩ ምድረ ወኵሎ ዓለመ ኢረከብኩ እግዚኦ ስመ ጥዑመ ዘእንበለ እግዚእየ ክርስቶስ ወኵሉ ረድኤት ወኵሉ ኃይል ዘዲበ ምድር ኢይከውን ዘእንበለ እመንገለ ስመ ኢየሱስ ክርስቶስ ኵሉ ዘመደ እጓለ እመሕያው እለ አሥመርዎ ለእግዚአብሔር እመንገለ ስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውእቱ ወኵሎ አም፡ኃ ክቡረ ወኄሩየ ኢነሣእነ ዘእነበለ እም ስመ ኢየሱስ ክርስቶስ። ሰማይኒ ወምድርኒ ኢፀንዑ እንበለ ሁከት ዘእንበለ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወስድስቱ ማየ መሳብክት ኢኮነ ወይነ ኄሩየ ዘእንበለ በስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወ፡ኃይላት ዐቢይት ወሊቃነ መላእክት ይሴብሕዎ ወይባርክዎ ለእግዚእነ ኢየሱስ

ክርስቶስ ሰማኒት ነፍስ ድኅኑ እማየ አይኅ እመንገለ ስመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐራ ሰማይ ወነገሥተ ምድርኒ ኵሎሙ ይትቀነዩ ለከ። ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ተስፋ መሢሐውያን። ኵሉ ነፍስ ያመልኩከ ወይባርኩከ። ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኵሉ ሕዝብ ኦርቶዶክሳያዊ ኅቡረ ይሴብሖ ወይባርኮ ለእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ። ስመ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእየ ይጥዕም እመዐቃውዓ መዓር ወሦከር። እስመ መዓርሰ ወሦከር ሶበ ይበልዑ እምኔሆሙ ይጸገቡ ወስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስሰ ኢይጸግቡ። ከናፍርየ ያንጠበጥባ መዓረ ሶበ እቤ ስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ ለመዓር ወለሦከር ወለመና አልቦሙ ጣዕም በኀቤየ እምስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ ስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ይኄይሰኒ ወይሄይስ እምኵሉ ፍጡር ዘታሕተ ሰማይ። ርኅራኄከ ብዙኅ ወኢይትነገር ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ዕውቅ ውእቱ ስምከ ውስተ አፈ ኵሉ ዘየአምን ብከ ወያፈቅረከ። ኵሉ ሰባሎ ዘሕግ አልቦ ውስቴቶሙ ዘይት ማስለከ ብርሃነ አዕይንትየኒ ወኃይለ ሥጋየኒ እምስምከ ቅዱስ ውእቱ። ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ረሲ ስመከ ቅዱሰ ሥዩመ ዘልፈ ውስተ አፉየ እስከ ተፍጻሜተ ሕይወትየ ኵሉ ነፍስ ክርስቲያን ኦርቶዶክሳውያን ኅቡረ ይባርኩ ወይሴብሑ ስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አሰስል እምኔየ ኵሎ መንፈሰ እከይ እንተ ዘኃጢአት። ተፈሥሑ ወተመክሑ ኵልክሙ መሢሐውያን በገነተ ስም መድኃኒነ ዘእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ። ጥዑም ውእቱ ስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይጥዕም እምፍሬ ገነት። ወበመዝሙር ቅዱስ እንተ አቡነ ዳዊት ንሴብሕ ወንዜምር ወንቄድስ ስመ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ። ከመ እባርክ ወእሴብሕ ስመከ መድኅነ። ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐውላዕሌየ ዐጋ ዓቢየ እንተ ዘመንፈስ ቅዱስ። ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ስድድ እምኔየ ኵሎ መንፈሰ ዘኢያሠምረከ እስእል ወእኀሥሥ እምኀቤከ። ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ግበር ምስሌየ ምሕረተ በመንግሥትከ።



## ትርጓሜ፡-

አማናዊ የእግዚአብሔር አብ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በመንግሥትህ ለእኛ ምሕረትን አድርግልን (ዮሐ 1፥29) የባሕርይ አባትህ እንዲህ ሲል ይመሰክርልሃል "አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድኩህ" (ማቴ 3፥16) ኪሩቤል በመንበርህ ሥር ይቆማሉ ሱራፌልም ሊመለከቱህ አይቻላቸውም (ኢሳ.6፥1-10) እኛ ግን በአርአያ ኅብስት በአርአያ ወይን በመልዕልተ መስቀል በዓይነ ኅሊና በተቀደሰው መሠዊያህ ላይ (ከመንበሩ) እናይሃለን ቅዱስ ሥጋህን ክቡር ደምህን እንቀበላለን አቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ መንፈሳዊ ምስጋና ሁሉ ለአንተ ይገባል። ዋጋው ከግምት በላይ የሆነ ነጋዴው (አማኒ) ያለውን ሁሉ ሸጦ የገዛው የከበረ ድንጋይ (እብነ ሕይወት) እሱ ነው፤ በውስጣዊ ሰውነታችን ይህ የከበረ ዕብነ ሕይወትነትህ እንዲያበራ አድርገው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ስምህ የነፍሳችን ሽልማት የልቦናችን ደስታ ነው፤ ኪሩቤል ክንፋቸውን ዘርግተው ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመሰግኑታል። ርኅሩኅ መሐሪ ይቅር ባይ የምሕረት አባት ሆይ ፀሐይ በጊዜው ይገባል፤ አንተ ግን ምንጊዜም አንተ ነህ አመቶችህም አያልቁም በቸርነትህ ብዛት ከሰማየ ሰማያት ወደኛ ወረድክ እንደ ጥበበኛ ባለመድኃኒትም አዳኝ በሆነ መለኮታዊ ጥበብሕ ደዌያችንን ሁሉ ፈወስክ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቸርነትን በተመላ በዓይነ ምሕረትህ ወደኔ ተመልከት። ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የጠላት የስንፍና መንፈስን ከእኔ አስወግድ አንተን እስብህ ዘንድ ንፁህ ልብን ፍጠርልኝ፣ አቤቱ ምድርን ዞርኩ ዓለምንም ሁሉ ተመለከትሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር ጥዑም ስም አላገኘሁም። ረድኤት ሁሉ ኃይልም ሁሉ በምድር ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በኩል ካልሆነ በቀር አይደረግም፤ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ የሰው ልጆች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በኩል ነው። የከበረና የተመረጠ እምነትና ክብርን ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም አላገኘንም ሰማይና ምድር ያለ ሁከት የፀኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ በስድስቱ የድንጋይ ጋኖች የተመላው ውኃ

የወይን ጠጅ የሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ ደጋግ ኃይላት ሊቃነ መላእክት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያመሰግኑታል፣ የሰማይ ሠራዊት የምድር ነገሥታት ሁሉ ለአንተ ይገዛሉ፣ የክርስቲያኖች ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ነፍስ ሁሉ ያመልክሃል፣ ያመሰግኑሃል። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ኦርቶዶክሳዊው ሕዝብ ሁሉ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ባንድነት ያመሰግነዋል ይባርከዋልም። የጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከመዓርና ከስኳር ይልቅ ይጥማል። የማር ወለላና ስኳር ከተመገቧቸው በኋላ ይጠገባሉ፣ ይሰለቻሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ግን አይጠገብም። የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በጠራሁ ጊዜ ከንፈሮቼ እንደማር የሚጣፍጥ ነገር ያንጠባጥባሉ። በእኔ ዘንድ ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም አንፃር ሲታዩ መዓር ወተት ስኳር መና ጣዕም የላቸውም ከምድር በታች ካለው ፍጥረት ይልቅ የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሻለኛል።

ርኅራኄህ ብዙ ነው አይነገርም፣ በሚወድህና በሚያምንህ ሁሉ ዘንድ ስምህ የታወቀ ነው። ያይኔ ብርሃን የሥጋዬ ኃይል ከቅዱስ ስምህ የተነሣ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቅዱስ ስምህ ዘወትር በአፌ ይሠየም (ይምላዕ ይጨመር አብዝቶ ይጠራ) እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ እንድጠራው፣ በቀናች ሃይማኖት የሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በኅብረት ፈጽመው የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ያመሰግናሉ። ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ኃጢአትን የሚያሠራ የሐኬት መንፈስን ሁሉ ከእኔ አርቅ።

የመሢሕ ወገኖች ሁላችሁ በዚህ መድኃኒትና ጌታ በሆነ ስም ደስ ይበላችሁ የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከፍሬ ገነት ይልቅ ይጥማል። ቅዱስ በሆነው በአባታችን በዳዊት መዝሙር የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ፈጽሞ እናመሰግናለን። መድኃኒት የሆነውን ስምህን አመሰግን ዘንድ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ታላቁን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በላዬ ላይ አፍስስ፤ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አንተን ደስ የማያሰኝህን መንፈስ ከእኔ አርቅልኝ።



ከአንተ ዘንድ ወደአንተ እለምናለሁ አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ ለእኔ ምህረትን አድርግልኝ አሜን!

ግብረ ሕማማት ገፅ 7-9

አንባቢ ሆይ ልዩ ስሙ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ተገንዘብ
አሜን ስለሕያው ስሙ ብሎ ይጠብቀን ይቀድሰን ያጽድቀን።
ከብዙ በጥቂቱ ከምልዑ በከፊሉ ኢየሱስ ማነው የሚለው ርዕስ ተፈጸመ።

## ጥያቄዎች

1. ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆኑ በምን ተገለጠ?
2. መለኮታዊነቱም የተገለጠባቸውን ስንት ነጥቦች አነበቡ?
3. ልዩ ስም ማለት ምን ማለት ነው?
4. ይህ ልዩ ስም የማን ስም ነው?
5. ስለዚህ ልዩ ስም ስንት ነጥቦችን አነበቡ?
6. በማጠቃለያው ላይ የተጠቀሰውን የቤተክርስቲያን መጽሐፍ ስም ከዚህ በፊት ያውቁታል? ማን ይባላል? ስለመጽሐፉ አጭር ማብራሪያ ከራስዎ ይጻፉ?

መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
U.S.A.